# ADDA BILISUMMAA OROMOO

**OROMO LIBERATION FRONT** **جبهة تحرير اورومو**

Gaafa: 12/09/2016 Date: تاريخ

Lakk.:017/stm/abo/2016 No.: رقم

## የኦነግ ስራ-ኣስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ መግለጫ

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ስራ-ኣስፈጻሚ ኮሚቴ ቋሚ ስብሰባውን ከመስከረም 1 እስከ 11 ቀን 2016ዓም በማካሄድ የድርጅቱ የስራ ዘርፎች ሪፖርት በማዳመጥ እንዲሁም፡ የኦሮሞ ህዝብ ነጻነትና የኦሮሚያ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ እየተካሄደ ስላለው ትግል ሁኔታ፣ ስለፋሽስቱ ወያኔ መንግስት፣ የጸረ-ፋሽስቱን ወያኔ እንቅስቃሴዎች፥ በኣማራ ክልል(ጎንደር፣ ጎጃምና ወልቃይት) ውስጥ እየተካሄደ ስላለው የህዝብ ኣመጽ፣ ስለኮንሶና መዠንግር፣ ስለጋምቤላ፣ ሲዳማ፣ ቤኒሻንጉል፣ ኦጋዴን፣ ስለኣፍሪካ ቀንድና ስለኣፍሪካ ኣህጉር እንዲሁም ስለኣለም ሁኔታ በቀጥታ ደግሞ ከኦሮሞ ህዝብ ነጻነትና የኦሮሚያ ሉዓላዊነት ጋር ተያይዞ የኦሮሞን የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ኣስመልክቶ በጥልቀት በመገምገም ከዚህ በታች ያሉትን ወሳኔዎች በማሳለፍ ስብሰባውን በስኬት ኣጠናቋል።

### ሰፊው የኦሮሞ ህዝብ

የኢትዮጵያ ኢምፓዬር ከተፈጠረችበት ጊዜ ኣንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ የኦሮሞ ህዝብ በጅምላ መገደል(የዘር-ማጥፋት)፣ ማንነቱን መነፈግ፣ መታሰር፣ መሰቃየት፣ መዘረፍና ከሃገሩ በሃይል ከመባረር በተረፈ በሃይል በተመሰረተችው የኢምፓየርነት ኣገዛዝ ውስጥ ያገኘው ይህ ነው የሚባል ኣንዳችም ፋይዳ የለም።
ይህንን የጨለመ የታሪክ ጉዞ ለመቀየር በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ውድ የኦሮሞ ልጆች ለዚህ ጀግና ህዝብ ነጻነትና ሉዓላዊነት መተኪያ የሌላትን ህይወታቸውን ኣሳልፈው ሰጥተዋል። የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ይህንን የጀግንነት ታሪክ በወረሱ የኦሮሞ ልጆች የተመሰረተው የኦሮሞ ህዝብ ከኣንድ ምዕተ-ዓመት ተኩል በላይ ለሚሆን ጊዜ እየከፈለ ላለው ከባድ መስዋዕትነት ፍሬ ለማስገኘት ነው። ኦነግ ባካሄደው ከባድ መስዋዕትነት ያስከፈለ መራር ትግል ዛሬ የኦነግ የፖለቲካ ፕሮግራም በኦሮሞ ህዝብ ድጋፍ ተቀባይነቱ እየጎላ መጥቶ በኢትዮጵያ ኢምፓዬር ውስጥ ላለው የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ ችግሮችና የባህል ጭቆና እንዲሁም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ዘላቂ መፍትሄ ለማስገኘት እየተቃረበ ይገኛል። ይህንን ለማድረግም የኦሮሞ ህዝብ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብና ከማዕከላዊ ኦሮሚያ ውስጥ በኣንድ ድምጽና የፖለቲካ ኣመለካከት ፋሽስታዊነቱ ካሁን በፊት ታይቶ የማይታወቀውን ጠላት ተጋፍጦ የጸረ-ጭቆና ኣመጽን ወደ የጭቆና ፍጻሜ ኣመጽ ትግል ኣሸጋግሮታል። ይህም ፍርሃትን በማሸነፍ ከኣባቶቹ በወረሰው ጀግንነት ጠላትን በመጋፈጡ ትግሉን ከመከላከል ወደ ማጥቃት ኣሸጋግሯል።

ኦነግ ባስቀመጠው እቅድና ፕሮግራም ላይ በመመርኮዝ የኦሮሞ ህዝብ ባዶ እጀቹን ለ11 ወራት በቀጣይነት እያፋፋመ ባለው የጭቆና ፍጻሜ ኣመጽ ያሳየውን ጀግንነትና ኣንድነት ያደንቃል። በዚህ ኣመጽ የኦሮሞን ህዝብ ነጻነትና የኦሮሚያን ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ፣ የኢምፓዬሪቷ ጠባቂ የሆነውን የወያኔ ፋሽስት መንግስትንና በኢምፓዬሪቷ ላይ የተመሰረተውን ስርዓት ከመሰረቱ መንቀል እጅግ ወሳኝ ነው። ይህም ነጻነቱን ባረጋገጠ ህዝብ፣ ነጻና ገለልተኛ በሆነ ህዝበ-ውሳኔ(ሬፈረንደም) ላይ የኦሮሞን ህዝብ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብቱን በማረጋገጥ እውን ይሆናል።

ስለሆነም የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ስራ-ኣስፈጻሚ ኮሚቴ ከዚህ ውጪ ሌላ መፍትሄ እንደሌለ ተገንዝቦና ተግባብቶ ይህን የጭቆና ፍጻሜ ኣመጽ በትጥቅና ትጥቅ ኣልባ የትግል ስልቶች በመጠቀም ይበልጥ እንዲፋፋም ኣስቸኳይ ጥሪ ያቀርባል። ይህ ፋሽስቱ የወያኔ መንግስት ወድቆ የኦሮሞ ህዝብ መብት እንዲረጋገጥ እስካሁን የሰጠውን ኣመራር በይበልጥ ኣጠናክሮ እንደሚቀጥል ኦነግ በድጋሚ ቃሉን ያድሳል።

## ለመላው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት፣ የኦነግ ኣመራሮች፣ ኣባላትና ደጋፊዎች

የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ኣባላት፣ የኦነግ ኣመራሮች፣ ኣባላትና ደጋፊዎች ለኦሮሞ ህዝብና ለኦሮሚያ ሉዓላዊነት እየተካሄደ ባለው ትግል ውስጥ ግንባር-ቀደም በመሆን እጅግ ፈታኝ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ውድ መስዋዕትነት እየከፈሉ ዛሬን መድረሳቸው የሚታወቅ ነው። ትግሉ ዛሬ የደረሰበት ደረጃና ህዝባችን ያለበት ሁኔታ በቆራጥነትና በቁርጠኝነት ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ሁሉ በመክፈል ትግሉን ከግቡ ለማድረስና የኦሮሞ ህዝብን የፖለቲካ ስልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ ባያለንበት ፋሽስቱን የወያኔ መንግስት በማጥቃት ላይ እንዲሰማራ መልዕክታችንን እናስተላልፋለን።

## ፋሽስቱን የወያኔ መንግስትና የስርዓቱን ተላላኪዎች በተመለከተ

ፋሽስቱ የወያኔ መንግስትና የወያኔ ተላላኪዎች የሆኑት በፌዴራል ደረጃና በኦሮሚያ ክልል ላይ ያሉት የኦፒዲኦ ኣመራር ኣባላት ኣብዛኛዎቹ ኣፋን ኦሮሞን የፊንፊኔ የስራ ቋንቋ ማድረግ፣ ከፊንፊኔ ኣካባቢ በሃይል ለተፈናቀሉ የኦሮሞ ዜጎች ቤት በመስጠት እንዲሁም መሰል እርምጃዎችን በማወጅ በትናንሽ የማስመሰያ ለውጦች ህዝቡን በማስገደድ ለስርዓቱ ድጋፍ እንዲወጣ ለማድረግ ኣቅደዋል። ይህ ለኦሮሞ ህዝብ ነጻነትና ለኦሮሚያ የሉዓላዊነት ጥያቄ ፈጽሞ ምላሽ ሊሆን የማይችል፡ የኦሮሞን ህዝብ ኣደናግረው የጭቆና ፍጻሜ ኣመጹን በማኮላሸት ጨቋኙን የወያኔ ስርዓት በኦሮሞ ህዝብ ጫንቃ ላይ ለማሰንበትና ለስርዓቱ ያላቸውን ታማኝነት ለማረጋገጥ የወጠኑት ጠላትዊ ሴራ መሆኑን እናስገነዝባለን።

ኦነግ በህዝባቸው ላይ የሚፈጸመው የዘር-ማጥፋት ወንጀል ተሰምቷቸው ወገናቸው እንዳይጎዳ ሲሰሩ የነበሩና ኣሁንም በመስራት ላይ ያሉትን የኦፒዲኦ ኣባላት ያደንቃል። የኦሮሞ ህዝብ ከላይ እንደተገለጸው የኦፒዲኦ ኣመራሮችና ጌቶቻቸው እየፈጸሙት ባለው ድብቅ ሴራ እንዳይታለሉ እያሳሰበ፥ የሕወሃት ፋሽስት መንግስት ያወጣውን ይህን እቅድ በማክሸፍ ለኦሮሞ ህዝብ ነጻነትና ኦሮሚያ ሉዓላዊነት እተካሄደ ያለውን ትግል በቆራጥነት በማጠናከር ለስርዓቱ ፍጻሜ እንድናበጅለት ኦነግ ኣጥብቆ ያሳስባል። ከዚሁ ጋር ከስህተታቸው ባለመማር በወገናቸው ላይ ወንጀል እየፈጸሙ ያሉ የኦሮሞ ዜጎችም ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ያስጠነቅቃል።

## በወያኔ መንግስት የጦር ሃይል ውስጥ ለሚገኙና በተለያዩ ደረጃዎች ባሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ለሚሰሩ የኦሮሞ ዜጎች በሙሉ

ሁሉም የኦሮሞ ዜጋ እንደሚያውቀውና እንደሚገነዘበው የዘር-ማጥፋት ወንጀል በኦሮሞ ህዝብ ላይ ከታወጀ ቆይቷል። ዛሬ የኦሮሞ ዜጎች ህይወት የወያኔ መሳሪያ ኢላማ መለማመጃ ሆናለች። ይህ ዘግናኝ እርምጃ ደግሞ ሁሉንም የኦሮሞ ዜጋ እንቅልፍና ኑሮ የሚነሳ መሆን ይገባዋል። ስለሆነም በወያኔ የጦር ሃይል ውስጥ የምትገኙና በፌዴራል ደረጃና በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በተለያዩ የመንግስት መዋቅሮች ውስጥ የምትሰሩ የኦሮሞ ተወላጆች እራሳችሁን በማደራጀት በምትችሉት ሁሉ ህዝባችሁ ለነጻነት እያካሄደ ካለው ትግል ጎን እንድትሰለፉ ኦነግ ወገናዊ ጥሪውን ያቀርባል። ይህንን ሃላፊነት ኣለመወጣት በኦሮሞ ህዝብና ከታሪክ ተጠያቂነት እንደማታመልጡ መገንዘብ ግዴታ ነው። ዛሬ ከኦሮሞ ነጻነትና ከኦሮሚያ ሉዓላዊነት ትግል ጎን የማንሰለፍ ከሆነ ከወገናችን ጋር የምንቆምበት ጊዜ መቸ ይሆን? የሚለውን ጥይቄ መምለስም ግዴታችሁ እንደሆነ ኦነግ ኣስረግጦ ያሳስባል።

## የኢትዮጵያን የፖለቲካ ድርጅቶች በተመለከተ

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጸረ-ፋሽስት ወያኔ የሆኑ የኢትዮጵያ ኢምፓዬር የፖለቲካ ሃይሎች ሁሉ እያካሄዱት ያለውን ትግል ያከብራል። በኢትዮጵያ ኢምፓዬር ውስጥ ለሚገኙ ህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት መከበር ዓላማ የሚታገሉ ድርጅቶችን ደግሞ ኦነግ በተለየ ይመለከታል። የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ(PAFD) የተመሰረተውም ለዚሁ ነው። በዚሁ ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ በሃገሪቱ ውስጥ በተጨባጭ መልኩ መሬት ላይ በሚታይ ስራ የሚታወቁ ድርጅቶች የየድርጅቶችን የፖለቲካ ዓላማ በማክበር፣ የጋራ ጠላት በሆነው ፋሽስት ወያኔ ላይ በማትኮር በጋራ ትግል እንድናስወግደው ኦነግ በድጋሚ ጥሪውን ያቀርባል።

**በተለያዩ ምክንያቶች ከድርጅታችን መዋቅር ውጪ ላላችሁ አባላትና ደጋፊዎች**

የኦሮሞን ነጻነትና የኦሮሚያን ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ እየተካሄደ ባለው ትግል የቀረው የስርዓቱ መውደቅ ኣይቀሬ መሆኑ እውን ቢሆንም ትግሉን ለማጠናቀቅ የሚጠበቅብን ኣስተዋጽዖ የላቀ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ ከፊታችን ያለውን ግዴታ በድል ለመቋጨት ኦነግ የሚሻውን ድጋፍ ከማድረግ የሚቆጥበን ማናቸውን ምክንያት መኖር የለበትም። ያለንበት ሁኔታ በመኖርና ኣለመኖር መካከል ኣንዱን እንድንመርጥ ያስገድደናል። ህዝባችንን ከመጥፋት ለመታደግ ያለንን የግል ችግር መፍታት ብልህነት መሆኑን በመረዳት ካሁን በፊት በተለያዩ ምክንያቶች ከኦነግ የወጣችሁ ኣባላትና ደጋፊዎች በኣፋጣኝ ወደ ድርጅቱ እንድትመለሱ ኦነግ ወገናዊና ሃገራዊ ጥሪውን ያቀርብላችኋል።

**ነጻ የሆኑ የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶችን በተመለከተ**

ጨቋኙ የወያኔ ፋሽስት መንግስትን ከኦሮሚያ በመንቀል የኦሮሞን ህዝብ ነጻነትና ዘላቂ ሰላም ለማስገኘት የኦሮሞን ህዝብ የሰው ሃይልና ሃብት በኣንድነት ማቀናጀት ወሳኝ መሆኑን በማመን ነጻ በሆኑ የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ከስምምነትና ከመግባባት መደረሱ ይታወሳል። ይህ መግባባትና ስምምነት በስራ እንዲተረጎም ከነዚህ ድርጅቶች ተወካዮች ተውጣጥቶ የተቋቋመው የኦሮሚያ ነጻነትና የኦሮሚያ ሉዓላዊነት ሃይሎች ኣስተባባሪ ኮሚቴ ይህንን ስምምነት ስራ ላይ ለማዋልና በመተግበሩ ስኬታማ እንዲሆን ኦነግ የሚጠበቅበትን እንደሚያበረክት ያረጋግጣል።

**በኣማራ ክልል (ጎንደር፣ ጎጃምና ወልቃይት) ኣካባቢ ያለውን እንቅስቃሴ በተመለከተ**

የኣማራ ህዝብ በጎንደርና በጎጃም ኣካባቢ እያካሄደ ያለው ጸረ-ወያኔ እንቅስቃሴ የሙብት እንቅስቃሴ መሆኑን ኦነግ ያምናል። ይሁን እንጂ የወያኔ መንግስት ካልተወገደ በስተቀር ይህ ጥያቄ ምላሽ ያገኛል ብሎ ኣያምንም። ስለሆነም በሁሉም ኣቅጣጫ የወያኔን መንግስት ለማንበርከክ መስራት ኣስፈላጊ መሆኑን ኦነግ እያስታወሰ፥ በፋሽስቱ ወያኔ መንግስት በኣማራ ክልል ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለውን ግድያ፣ እስራትና ሰቆቃ በጥብቅ ያወግዛል።

በወያኔ መንግስት የሚፈጸመውን ዝርፊያና ማንነታቸውን የማጥፋት እርምጃ በመቃወም የኮንሶና የመጀንግር ህዝቦች እያካሄዱት ያለውን ትግል የኦሮሞ ህዝብና መሪ ድርጅቱ ኦነግ እያደነቀ፥ ከጎኑም እንደሚቆም ያረጋግጣል። የኮንሶና የመጀንግር ህዝቦች እያካሄዱት ያለው ትግል ፍትሃዊ ትግል ነው ብሎም ያምናል። በተጨማሪም በኮንሶና መጀንግር ህዝቦች ላይ እየደረሰ ያለውን የጅምላ ግድያ፣ እስራትና ወከባ ኦነግ በጥብቅ ያወግዛል።

**በውጪ ሃገራት የሚገኘውን የኦሮሞ ማህበረሰብን በተመለከተ**

የሃገር ባለቤትነት መብቱን በመነፈግ፣ በሰላም መኖር ባለመቻሉ በተለያዩ ሃገራት የሚኖረው የኦሮሞ ማህበረሰብ ለስደተኝነት የዳረገውን ምክንያት በሚገባ ተረድቶ ሃገሩን ማስመለስ ወሳኝ መሆኑን ኣምኖ ለኦሮሞ ነጻነትና ለኦሮሚያ ሉዓላዊነት ትግል ድጋፍ ሲያደርግ ከዛሬ ደርሷል። ኦነግ ይህንን ኣስተዋፅዖ እያደነቀ ትግሉን በድል ለመቋጨት ኣሁን ያለው ሁኔታ የሚጠይቀውን ልዩ ግዴታ ለመወጣት በውጪ ሃገራት ያለው ማህበረሰባችን ለትግሉ የሚያደርገውን ድጋፍ በእጥፍ-ድርብ እንዲያሳድግ የኦነግ ስራ-ኣስፈጻሚ ኮሚቴ ጥሪውን ያቀርባል።

**የወያኔ መንግስት እያካሄደ ያለውን የዘር-ማጥፋት(Genocide) በተመለከተ**

ፋሽስቱ የወያኔ ሕወሃት መንግስት በኢምፓዬሪቷ ውስጥ ከታዩት መንግስታት ሁሉ በላቀ ሁኔታ በጭካኔ የተሞላ መሆኑን ድርጊቱ እንደሚያረጋግጥ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የሚታገሉ ድርጅቶች ሁሉ እየመሰከሩ ነው።
የዘር-ማጥፋት ወንጀሉ በቀጥታ በኦሮሞ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ መሆኑም ፋሽስቱ ወያኔ ላለፉት 11 ወራት የፈጸመውን ተግባር መመልከትና የወሰደውን እርምጃ ማጤን በቂ ነው። ይህ የዘር-ማጥፋት በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል፣ በሲዳማ፣ በኦጋዴንና በኮንሶና በመጀንግር ህዝቦች ላይም በስፋት ሲፈጸም የነበረና ኣሁንም እያተፈጸመ ያለ ወንጀል ነው። በቅርቡ ደግሞ በኣማራ ህዝብ ላይ ያነጣጠረውን ግድያ ማስተዋሉ ተጨማሪ ማስረጃ ነው ብለን እናምናለን።
ስለሆነም ይህንን እየተፈጸመ ያለውን ዘግናኝ ግድያ ነጻና ገለልተኛ የሆነ ቡድን መርምሮ በማጣራት ለተባበሩት መንግስታትና ለኣለምኣቀፉ የወንጀለኞች ችሎት(ICC) እንዲያቀርብ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ይጠይቃል። ከዚሁ ጋር በኦሮሞ ህዝብና በሌሎች ህዝቦች ላይ እየተፈጸመ ያለው የዘር-ማጥፋት ወንጀል መሆኑን ተገንዝበው ኣቤቱታቸውን በማቅረብ ላይ ላሉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ኦነግ ያለውን ኣድናቆትና ምስጋና እየገለጸ ይህንን የተቀደሰ ስራቸውን ኣጠናክረው እንዲቀጥሉ ይጠይቃል።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ !!!**
**የኦነግ ስራ-ኣስፈጻሚ ኮሚቴ**

**መስከረም 12, 2016ዓም**